# <u>አገር፣ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት</u>
# <u>ምንጊዜም ድል አድራጊ</u>
# <u>የማይበገር ኃይል ነው</u>

*ከአስተዋይ በቀለ*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው መላ-አገሩን፣ ሰንደቅ አላማውን፣ አንድነቱን፣ ደህንነቱን፣ መብቱን፣ እድገቱን፣ ብሔራዊ ግሥጋሴውንና ኢትዮጵያዊነት ነው።*

*ይኽ ወይም ይህ አልገባኝም የሚል ካለ ሕዝቡንና ፍላጐቱን ጨርሶ የሚያውቅ ገልቱ ወይንም ደግሞ ሆን ተብሎ በተሰላ የፖለቲካ ሸፍጥ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የካደ ባንዳና ደመኛ ጠላት ነው። እነዚህ ጠላቶች በያይነቱ ናቸው።*

*ሕዝቡን ሳያውቁ፣ ተጠግተው ሳይኬውንና ፍላጐቱን ሳይረዱ እናውቅልሃለን በማለት የውጭ ርእዮተ- ዓለም አናቱ ላይ መቸለስና እሱ በማያውቀው ባልተወያየበትና ባላፀደቀው ባዕድ ሕገ-መንግሥት፣ እንደ ጋሪ ዓይኑንና ልቦናውን ጋርዶ እያስራቡት ረግጠው ቼ በለው ማለት የሕዝብ የበላይነትን አለመቀበልና ይባስ ብሎ አበሳ መከራውን ማሳየት ነው።*

*ካሁን በፊት በዘመነ-ወታደር፣ ሕዝብ እባካችሁ ኅብረተሰባዊነት አይሰራም፣ ግራ እጅ አንሱ አትበሉን፣ ግራ ልግመኛ ጐደሎ ነው እረፉ ቢልም፤ ደርግ የፓሪስ ላቲን ኳርተር የቀፈቀፉቸውን አናርኪስቶች ይዞ ሶሻሊዝም በማወጅ አገርና ትውልድን አጠፉ።*

*ወያኔ ደግሞ ይባስ ብሎ አገሪቱን እንደ ባቢሎን ግንብ ቆጥሮ በግንጠላና በክልል ቦጫጭቆ ሕዝብን ወግድ ብሎ እየፈጀና እያተራመሰ ነው።*

*የሥልጣን ጥመኛው ደግሞ ሊበራሊዝም ናዚዝምንና ፋሺዝምን በአውሮፓ የወለደ ደካማ ርእዮት መሆኑን ባለመገንዘብ፣ ገና ምኑንም ሳይዘው ሊበራል ዲሞክራሲ እያለ ያፋጫል።*

*ተለጣፊው ለይቶለት ከወያኔ ጋር ሰልዳሬ ሆኖ አብሮ ወይኗል። የአዲስ አበባ ኗሪ ተቃዋሚዎችም ደግሞ ሁሏም ለወያኔ አጐብድዳ ጥቅሟን እያሳደደች ነው።*

*መንገድ የጠፋቸው ገልቱ የውጭ ቅጥረኞች ደግሞ የምን ኢትዮጵያ! የምን አንድነት! የምን ኢትዮጵያዊነት! እያሉ ጠባብነትን በባንቱስታን ኬሻቸው ውስጥ እንዲያው በከንቱ ልፉ ብሏቸው ይጐሰጉሳሉ።*

አምስተኛ ረድፍ ሰላይና ባንዳው ደግሞ አገርንና ሕዝብን ሙልጭ አድርጐ ክዶ ሰላቢ አጋንንት ሆኗል።

አደርባዩና ገንዘብ አፍቃሪው ደግሞ የአገርና የሕዝብን ችግር እንዳይሰማ የሰለሞን ተካልኝን ዘፈን ብቻ እያዳመጠና ብሩን እየኰተኰተ በማካበት ለወያኔ እድሜ ይለምናል።

ለአገር፣ ለሕዝብና ለኢትዮጵያዊነት ፀንቶ የቆመ ታጋይ ድርጅት አንድ ብቻ ነው። ይህ ድርጅት በፅኑ የትግል አቋሙ ዛሬ ሕዝብ ውስጥ ለመቀጣጠል በቅቷል።

ከዚህ ድርጅት ውጭ ያሉት ተቃዋሚዎች ኢትዮጵያ የሚሏት ወያኔ ከማይ አንበሳ በታች ካለሕዝብ ሪፈረንደም የፈጠራትን ግማሽ ኢትዮጵያን ብቻ በመሆኑ ሕዝብ ይጠላቸዋል። የኤርትራን መገንጠል በመቀበላቸውና ለኢትዮጵያ የማይገሰስ ሕልውና የወደቁትን የሰማዕታት አጽም በማራከሳቸው በባንዳነት/ከሀዲነት ፈርጇቸዋል። አሁን በተቃውሞ ፖለቲካ ሽፋን ፌር-ፌር ቢሉም፣ ነገ ጧዋት ሕዝብ እንደ ቢራቢሮ እየለቀመ በትሪዝን እንደሚጠይቃቸው የብስጭቱ ግለት መዝግቧቸው ጊዜ ይጠብቃል።

የኢትዮጵያ አባጣ-ጐርባጣ መልክዓ-ምድር በመገናኛ ድቀት ያቆየውን ቋንቋ ለራሳቸው የጐሣ ስምና መለዮ አድርገው ኢትዮጵያዊነትን ስለካዱበት ሕዝብ ጠባቦችንና የጐሳ ተብዬ አስገንጣዮችን ጨርሶ አይፈልጋቸውም። እንደ ጠላ ገፈት እፍ ብሎ ገፎ ሊጥላቸው፣ ለይቶ በስምና በመልክ አውቋቸዋል።

**ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በረጅም ዘመን አኩሪ ታሪክ በሕዝብ የተገነባ ሕልውና ስለሆነ እንኳን ለአገር ውስጥ ለውጭ ወራሪና አስወራሪ ጠላት እንኳ ያልተበገረና የማይበገር አልፋ-ኦሜጋ ነው።**

**የርዕዮተ- ዓለማችንና የእድገታችን ምንጭና መሰረቱ አገር፣ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት ነው።**

**ወያኔንም ሕልውና አሳጥቶ ድራሹን የሚያጠፋው ኃይል አንድ አገር ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት ነው።** ሁሉን ያቀፈ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኅብረት ይህን እስካልተገነዘበና እስከልተቀበለ ድረስ ሊመሰረት አይችልም። ምንጊዜም አንድ አገር፣ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት ካለጥርጥር ዛሬም-ነገም በቀጥታ ያሸንፋል።